# የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የጥራት ስራ አመራር ISO 9001:2008 ሰርተፍኬት ተሰጠዉ፡፡

አዲስ አበባ የካቲት 2008 ዓ.ም፡ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከአለም አቀፉ የደረጃዎች ድርጅት ISO 9001:2008 የጥራት ስራ አመራር ሰርተፍኬት አገኘ፡፡

የተሰጠዉ ሰርተፍኬት የኢንስቲትዩቱን ሁሉንም አገልግሎቶች የተመለከተ ሲሆን ፣ የኢንስቲትዩቱን ሁሉንም የስራ ሂደቶች በዉስን ፕሮሲጀሮች ወይም የአሰራር ቅደም ተከተሎች ለማሻሻልና ለመለካት ያስችላል ይህም ደንበኞች ቀጥተኛ የሆነ አገልግሎትና ድጋፍ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ISO 9001:2008 የጥራት ስራ አመራር ስርዓትን ለመዘርጋት የደንበኞችን እርካታ በማረጋገጥና የሚሰጣቸዉን አገልግሎቶች ጥራትና ተዓማኒነት በማሻሻል ከሶስት አመታት በፊት ጀምሮ በቁርጠኝነት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በየካቲት 2008 ዓ.ም በሰርተፍኬት ሰጪዉ አካል የተደረገዉን ኦዲት በብቃት በማለፍ ለሁሉም የስራ እንቅስቃሴዎቹ ደረጃቸዉን የጠበቁ ለመሆናቸዉ የISO 9001:2008 የጥራት ስራ አመራር ስርዓት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ባለቤት ለመሆን በቅቷል ፡፡

ሰርተፍኬቱ ከፈረንጆቹ የካቲት 18 2016 ጀምሮ እስከ መስከረም 14 2018 ድረስ የፀና መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማኔጅመንት መላዉን ሰራተኞች ፣ ተባባሪዎችና አጋሮች ለዚህ ስኬት በማድረሳቸዉ ምስጋናዉን ይገልፃል፡፡